*የፈላ ውሃ መረጃ መስጫ የበር ላይ ተንጠልጣይ*

**የፈላ ውሃ መረጃ መስጫ ማስታወቂያ**

**London Park Towers Apartments** በውሃ ግፊት ላይ በተፈጠረው ከፍተኛ ቅናሽ ምክንያት የፈላ ውሃ ማስታወቂያ አውጥቷል። በአካባቢያችሁ በሚካሄደው የውሃ መስመር ጥገና ምክንያት የውሃ አገልግሎታችሁ በጊዜያዊነት ተቋርጦ ነበር።

ይህ ለቅድመ ማስጠንቀቂያ የተሰጠ የፈላ ውሃ መረጃ መስጫ ማስታወቂያ የሚጀምረው:-
ቀን:-8/10/2023_____ ሰዓት:- 09:00 am

ለደህንነት ቅድመ ጥንቃቄ ሲባል፣ የፈላ ወይም የታሸገ ውሃ ለመጠጥ፣ ፈሳሽ ምግብና ለምግብ ዝግጅት እና በረዶ ለመስራት ጥቅም ላይ መዋል አለበት። ውሃን ማፍላት በውስጡ የሚገኙ ባክቴሪያዎችና ሌሎች ነፍሳትን ይገድላል። ማፍላት የቧንቧ ውሃ ለመጠጥ አስተማማኝ መሆኑን ለማረጋገጥ ተመራጭ ዘዴ ነው። ሁሉንም የቧንቧ ውሃ ወደ ድስት ያምጡ፣ **ለአንድ (1) ደቂቃ ያፍሉት** እና ከመጠቀምዎ በፊት እንዲቀዘቅዝ ያድርጉ ወይም የታሸገ ውሃ ይጠቀሙ።

ውሃቸውን ማፍላት የማይችሉ ደንበኞች፣ እንደ አማራጭ የማንጻት ዘዴ፣ ውሃን ከብክለት ለማጽዳት ፈሳሽ የቤት ውስጥ ማጽጃ መጠቀም ይችላሉ። የውሃ ማጣሪያው ምርት በቅርብ ጊዜ የተገዛ፣ ከተጨማሪ ግብዓቶች እና ሽታዎች የጸዳ እና ቢያንስ 5.25% ሃይፖክሎራይት ውህድ መያዝ አለበት። የማህበረሰብ ጤና ባለስልጣናት በእያንዳንዱ ጋሎን ውሃ ውስጥ 8 ጠብታዎች (¼ የሻይ ማንኪያ) ማንጫ ወይም ብሊች እንዲጨምሩ ይመክራሉ። ከመጠቀምዎ በፊት ውሃው መማሰል እና ቢያንስ ለ 30 ደቂቃዎች እንዲቆም መደረግ አለበት። የአምራች ድርጅቱን መመሪያዎች በመከተልም የውሃ ማጣሪያ ከኒኖች መጠቀም ይቻላል።

**የ London Park Towers Apartments ሰራተኛ** በአካባቢው የሚኖሩ ደንበኞችን የአገልግሎት መቋረጥ ያስከተለውን ብልሽት ለመጠገን እየሰራ ነው። ይህ ሁኔታ ላስከተለው ማንኛውም ችግር ይቅርታ እንጠይቃለን፣ እናም በዚህ ክስተት ወቅት ላደረጉት ትብብር እናመሰግናለን።

ከታች ያሉትን መመሪያዎች እንዲከተሉ እንመክራለን:-

1- የተለመደው የውሃ ግፊትዎ ከተመለሰ በኋላ ወዲያውኑ ንጹህ ውሃ ከውኃ ቧንቧዎችዎ ውስጥ እስኪፈስ ድረስ የውስጥ ቧንቧ መስመሮችዎን በውሃ ያለቅልቁ
2- የመጠጥ ውሃን ከመጠጣትዎ በፊት ለአንድ ደቂቃ ያህል ያፍሉት
3- **የባክቴሪያ ምርመራ እስኪጠናቀቅ ድረስ እና መረጃ መስጫ ምክሩ መሰረዙን እስኪገልጽልዎ ድረስ** ይህ ምክር በሥራ ላይ ይቆያል (በአጠቃላይ፣ የውሃ ምርመራን ለማጠናቀቅ ወደ ሁለት ቀናት አካባቢ ይወስዳል)።

እባክዎ ይህን ውሃ ለሚጠጡት ሁሉ በተለይም ይህ ማስታወቂያ በቀጥታ ላልደረሳቸው (በአፓርትመንቶች፣ በአረጋውያን መንከባከቢያ ቤቶች፣ ትምህርት ቤቶች ወይም የንግድ ተቋማት ውስጥ ያሉ ሰዎች) ሌሎች ሰዎች ሁሉ ይህን መረጃ ያካፍሉ። እባክዎ ይህን ማስታወቂያ በሕዝባዊ ቦታዎች ላይ ይለጥፉ ወይም ቅጂዎችን በእጅ ወይም በፖስታ ቤት በኩል ያሰራጩ።

ለተጨማሪ መረጃ፣ እባክዎ ወደ London Park Towers Apartments በስልክ ቁጥር 1-833-202-8964 ይደውሉ